# የሃይል እርምጃ መቸውም ቢሆን ለፖለቲካ ችግር መፍትሄ ኣይሆንም!

*የኦሮሞ ነጻነት ግንባር መግለጫ*

የኢትዮጵያ ህዝቦች በወያኔ ኣገዛዝ ስር ከሚደርስባቸው የከፋ ሰቆቃ የተነሳ በተለያዩ ጊዜያት ተቃውሞኣቸውን በተለያየ መልኩ ሲያሰሙ ዛሬን ደርሰዋል። ዲሞክራሲያዊ ኣስተዳደር ከመዘርጋት፡ ስልጣን ላይ ያለው ቡድን ኣምባገነናዊነትን በማስፈኑ፤ ህዝቦች እኩልነትን ተነፍው የኣናሳ ቡድን የበላይነት እውን መሆንና፡ በገድብ-የለሽ ዝርፊያ ድሕነት መንሰራፋት፥ የኢትዮጵያን ህዝቦች ኣንቀው የያዟቸውና ለሰቆቃ ኑሮ የዳረጓቸው ችግሮች ናቸው። በተለይ የኦሮሞ ህዝብ ለጭቆና ከተዳረገበት ወቅት ወዲህ ሰብዓዊ ፍጡር ሊሸከመው በማይችል መከራ እየተንገላታ ይገኛል።

እነዚህን ችግሮችን ለመፍታት በሰላማዊ መንገድ የሚቀርብ ጥያቄ ሰሚ ጆሮ በማጣቱ ህዝቡን ትዕግስት ኣስጨርሶ፡ ወደ ኣመጽ በመቀየር የሰው ህይወትና ንብረት ሲያጠፋ እንደነበርና ኣሁንም እያጠፋ መሆኑ ከማንም የተሰወረ ኣይደለም። ህዝቦች መብቶቻቸውን በሰላማዊ መንገድ ለማስከበር ያደረጓቸው ጥረቶች በወያኔ ዘንድ ተቀባይነት ኣጥቶ፡ ግድያ፤ እስራትና የተለያዩ ሰቆቃዎችን በመፈጸም ህዝቦችን ለባሰ ኣስከፊ ጉዳት መዳረግና ማዋከብ ስልጣን ላይ ባለው ስርዓት እየተወሰደ ያለ እርምጃ ነው። ስርዓቱ ኣሁንም ሌላ መፍትሄ እየታየው ኣለመሆኑን፡ በኦሮሞ ወጣት ተማሪዎችና በህዝቡ ላይ እየወሰደ ባለው ጭካኔያዊ እርምጃ በማያወላዳ መልኩ ኣረጋግጧል።

የወያኔ መንግስት የኦሮሞ ተማሪዎችና ህዝቡ በሰላማዊ መንገድ ላቀረቡት ጥያቄ፡ በሰላማዊ መንገድ ምላሽ ከመስጠት፡ የሃይል እርምጃን መርጦ በጠራራ ጸሃይ በወሰደው እርምጃ በኣስሮች የሚቆጠሩ ኦሮሞ ዜጎችን ገድሎ፡ ሌሎች በኣስሮች የሚቆጠሩትን ደግሞ ማቁሰሉና በርካታ ሃብት ማውደሙ ባለፈው ሳምንት በኦሮሚያ የተለያዩ ኣካባቢዎች የተፈጸመ፡ ሁሉም ያየውና የሰማው እውነታ ነው። በዚህ ጭካኔያዊና ፋሽስታዊ እርምጃ ሊረክካ ያልቻለው የወያኔ መንግስት፡ ህዝቡን ይበልጥ የሚያናቁርና ጠላትነትን የሚያባብስ እርምጃ እየወሰደ መሆኑ ደግሞ ሌላው በገሃድ እየታየ ያለ ሃቅና የስርዓቱን ማንነት ይበልጥ የሚያረጋግጥ ነው።

በኣናሳ ቡድን የሚመራው ይህ ስርዓት ከተስፋ መቁረጥና ፍራቻ፡ የትግራይ ብሄር ተወላጅ የሆኑትን ተማሪዎችና ህዝቡን ወደ ማስታጠቅ መሸጋገሩ፡ በህዝቦችን መካከል ያለው ግንኙነት ወዴት ሊያመራ እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል። በተለይም ከትግራይ ህዝብ ውስጥ ወንዶችን በፊንፊኔ ውስጥ በየቀበሌው ከቻይና የገዛውን (AKM- Sniper የተባለ)ክላሽ ጠብመንጃ በነፍስ ወከፍ እያስታጠቀ ይገኛል። ይህ ድርጊት ወያኔ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ችግር ወደ ባሰ ኣስጊ ደረጃ እያሸጋገረው መሆኑን ያሳያል። ከዚህም ሌላ የወያኔ መንግስት በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች በትምህርት ገበታ ላይ ያሉ የኦሮሞ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ትተው እንዲሄዱ ከፍተኛ ጫና ከማሳደሩም በተጨማሪ፡ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ይዘቶቻቸው የኦሮሞን ጉዳይ የሚዳስሱ መጽሃፍትን ለይቶ እያጠፋ ነው። እነዚህም ድርጊቶች የተስፋ መቁረጥና ጠላታዊ እርምጃዎች መሆናቸው ኣያጠያይቅም።

የኦሮሞ ነጻነት ግንባር የወያኔ ስርዓት በኦሮሞ ዜጎችና በሌሎችም ህዝቦች ላይ እየወሰደ ያለውን እርምጃዎች በጽኑ እያወገዘ፡ ይህ እርምጃ በኦሮሞ ህዝብ ብቻ ሳይሆን የመብት ጥያቄ ባነሱ ዜጎች ሁሉ ላይ ያነጣጠረ መሆኑን ያስገነዝባል። በተወሰደው እርምጃ ለሚፈስሰው የህዝብ ደም ተጠያቂው ስርዓቱ መሆኑን ከወዲሁ እያሳወቀ፡ ሁሉም የሃገሪቷ ዜጎች ይህንን ህዝቦችን በመለያየት የጦር መሳሪያ የማደሉን ድርጊት እንዲያወግዙ ያሳስባል።

በኦሮሚያ ውስጥ የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች የወያንኔ መንግስት እያስታጠቃቸው ያለው የጦር መሳሪያ ለሌላ ኣስከፊ ኣደጋና ወንጀል ከመዳረግ ኣልፎ፡ እንደማይፈይዳቸው እያሳሰበ፡ መሳሪያውን እንዲመልሱ ጥሪውን ያቀርባል። ዋስትናችሁ ኣብራችሁ ከኖራችሁት ህዝብ ጋር ሰላምን ማስገኘትና ለጸረ-ህዝብ መንግስት ማገልገል ማቆም ብቻ መሆኑን ያስገነዝባል። የወያኔ መንግስት ባሁኑ ወቅት የኦሮሞ ህዝብ እያቀረበ ላለው ጥያቄ ኣጥጋቢ ምላሽ ከመስጠት በስተቀር ማንኛውንም ኣይነት የሃይል ኣርምጃ መውሰድ መፍትሄ ሊሆን እንደማይችል የኦሮሞ ነጻነት ግንባር በድጋሚ ኣጥብቆ ያሳስባል።


P.O. Box 6973 Asmara, Eritrea Tel 2911 153886 Email: abo.abo976@gmail.com, *www.oromoliberationfront.org*

የኦሮሞ ነጻነት ግንባርና የኦሮሞ ህዝብ እያካሄዱት ያለው ትግል የራስን መብት ለማስመለስና ጨቋኝ ስርዓትን ከጫንቃው ላይ ኣሽቀንጥሮ ለመጣል መሆኑን ለመላው ህዝቦች በዚህ ኣጋጣሚ ይገልጻል። ለኦሮሞ ነጻነት የሚካሄድ ትግል በማንኛውም ህዝብ ላይ ያነጣጠረ ኣይደለም። በ1976ዓም በጸደቀው የኦሮሞ ነጻነት ግንባር የፖለቲካ ፕሮግራም ላይ ኦነግ ከመጀመሪያ ኣንስቶ በግልጽ እንዳስቀመጠው፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ህዝቦች የኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግል ኣጋሮች ናቸው። ነጻነቷ በተረጋገጠ ኦሮሚያ ውስጥም የሃገሪቷን ህገ-መንግስትና ህጎች የሚያከብር፡ ማንኛውም ዜጋ ልዩነት ሳይደረግበት የመኖርና የመስራት መብት ኣለው። ስለሆነም ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝቦች ከዚህ በተቃራኒ በጨቋኙ ስርዓት በሚነዛው ፕሮፓጋንዳ ሳይደናገሩ ከጨቋኙ የወያኔ ስርዓት ጋር በትንቅንቅ ላይ ላለው የኦሮሞ ህዝብ የነጻነት ትግል ሙሉ ድጋፋቸውን እንዲለግሱ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር ጥሪ ያቀርብላቸዋል።

በሃገር ቤትና በተለያዩ ውጪ ሃገራት ያለው የኦሮሞ ማህበረሰብ ባጠቃላይ የኦሮሞ ህዝብ፡ መብቱን ለማስከበር ይዞት ለተነሳው ፍትሃዊ ጥያቄ እጅ ለእጅ ተያይዞ በመነሳት፡ ከኣንድ ምዕተ-ዓመት በላይ የተጫነበትን የጭቆና ቀንበር ከላዩ ላይ ለማሽቀንጠር እንቅስቃሴውን እንዲያፋፍም የኦሮሞ ነጻነት ግንባር በኣጽንዖት ያሳስባል።

**ድል ለኦሮሞ ህዝብ!**

**የኦሮሞ ነጻነት ግንባር**

**ግንቦት 5, 2014**